# ነፃ ስልጠና በኖርዌጅኛ ቋንቋ እና በህብረተሰብ ትምህርት

**የኖርዌጅኛ ቋዋንቋዋ እና የህብረተሰብ ትምህርት ስልጠና በነፃ ስለማግኘት መብት**

በኖርዌይ ኣገር የመኖሪያ ፈቃድ ሲያገኙ በጠቅላላ ለ600 ሰዓታት ያህል ስልጠና ፥ ማለትም፤

♦ለኖርዌጅኛ ቋዋንቋዋ 550 ሰዓታት እና

♦ለህብረተሰብ ትምህርት 50 ሰዓታት ነፃ የስልጠና መብት ይኖረዎታል ።

ስልጠናው ለሶስት ዓመታት ያህል በነፃ የሚሰጥ ሆኖ ተግባራዊ የሚሆነው ፥

♦የመኖሪያ ፈቃድ ካገኙበት ቀን ጀምሮ ወይም

♦ወደ ኖርዌይ ህጋዊ ፍቃድ ይዘው ከገቡበት ቀን ኣንስቶ ሊሆን ይችላል።

እላይ በተጠቀሱት ሶስት ዓመታት ስልጠናዉን ካልጀመሩ ወይም ካላጠናቀቁ ስልጠናውን ከፍለው እንዲወስዱት ይደረጋል ።

**የኖርዌጅኛ ቋዋንቋዋ እና የህብረተሰብ ትምህርት ስልጠና ስለመውሰድ ግዴታ**

የኖርዌጅኛ ቋዋንቋዋ እና የህብረተሰብ ትምህርት ስልጠናውን በ600 ሰዓታት የማጠናቀቅ ግዴታ የሚያስፈልገው፥

♦ቋዋሚ የነዋሪነት ፈቃድ እና /ወይም

♦የዜግነት መብት ለማግኘት ማመልከቻ ለማቅረብ ይሆናል ።

ይህ የስልጠና ግዴታ በምዝገባ ወቅት ዕድሜዎ 55 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ግን ተፈፃሚነት ኣይኖረውም ።

ከስልጠናው ግዴታ ነፃ ለመሆን ማመልከት የሚችሉት፥

♦የኖርዌጅኛ ወይም የሳሚኛ ቋዋንቋዋ በቂ ችሎታ ያሉዎት መሆኑን የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ የሚችሉ ከሆነ ወይም

♦በተለይ ደግሞ የጤና እክል ወይም ሌላ ኣሳማኝ ምክንያት ካለዎት ይሆናል ።

**ተጨባጭ መረጃ**

ስልጠናውን ለመውሰድ ወይም ላለመውሰድ መረጃ ከፈለጉ በተመዘገቡበት የህዝብ ምዝገባ ፅህፈት ቤት ኣቅራቢያ በሚገኘው የማዘጋጃ ቤቱ /ኮሚን/ የጎልማሶች ማሰልጠኛ ማእከል በኣካል ቀርበው ማመለከት ይችላሉ ። የምዝገባ ቀን ማጠናቀቂያ ለማወቅ ወይም መብትዎን በተመለከተ ጥያቄ ካለዎት ወይም መረጃ ከፈለጉ ከማሰልጠኛ ማእከሉ ጋር መገናኘት ይችላሉ።

ተጨማሪ መረጃ ከሚከተሉት ድረገፆች ማግኘት ይችላሉ።

www.imdi.no እና www.udi.no.